# በእነ አቶ ሀይሉ ሻውል የወንጀል ክስ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን የማሰማት ሂደት

በእነ አቶ ሀይሉ ሻውል ጉዳይ 111 ተከሳሾቸ ላይ የቀረቡት ክሶች ይዘት፡ጠ

1ኛ ሀገ መንግስቱንና ሀገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ወንጀል፣ 2ኛ በሀገ መንግስቱ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባሩን እንዳያከናውን የማሰናከል የወንጀል ድርጊት መፈፀም፣ 3ኛ በመንግስት ላይ የትጥቅ አመፅ የማነሳሳት የማደራጀትና የመምራት ወንጀል መፈፀም፣ 4ኛ የሀገር መከላከያ ሀይልን የመጉዳት ወንጀል መፈፀም፣ 5ኛ በሀገር ላይ ከፍ ያለ ክዳት ወንጀል መፈፀም፣ 6ኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ክሶች መሆኑ ይታወሳል።

በእነዚህ ክሶቸ ላይ ዐቃቢ ህግ የቪድዮ፣ የኦደዮ፣ የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርቧል። አብዛኞቹ ተከሳሾቹ ምንም እንኳን ጠበቃ አቁመው የመከራር መብታቸውን በፍቃዳቸው የተዉ ቢሆንም በዐቃቢ ህግ የማስረጃ የማሰማት ሂደት ተከሳሾቹ ሲከራከሩ መቆየታቸው ይታወቃል።

ፍርድ ቤቱ ከመጋቢት 21ሐ1999 ዓ.ም ጀምሮ ብይን መስጠት ጀምሯል። እስካሁን በደረሰው ሂደት በአንደኛው ክስ ማለትም ሀገ መንግስቱንና ሀገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ወንጀል ላይ ክስ ከቀረበባቸው 111 ተከሳሾች ላይ በሰጠው ብይን መሰረት የሰኔ 1ሐ1997 እና የጥቅምት 1998 አመፅ ሀገ መንግስቱንና ሀገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ድርጊት መሆኑን፣ ቅንጅትና በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰቡ ተከሳሾች ለአመፁ መነሳት ምክንያቶች እንደሆኑ አረጋግጠ፣ ለዚህም ተጠያቂ ናቸው በማለት ተከላከሉ ያላቸው ተከሳሾች፡

1. አቶ ኃይሉ ሻውል
2. አቶ አባይነህ ብርሃኑ
3. ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ
4. አቶ ግዛቸው ሽፈራው
5. ዶር ኃይሉ አርአያ
6. አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል
7. አቶ ስለሺ ጠና
8. ዶር ብርሃኑ ነጋ

9. ዶር በፈቃዱ ደግፌ
10. ፕር መስፍን ወሐማርያም
11. ዶር ያዕቆብ ኃሐማርያም
12. ወሐት ብርትኳን ሚደቅሳ
13. አቶ አስቻለው ከተማ
14. ዶር ታዴዎስ ቦጋለ
15. አቶ ገሐፃድቅ ኃሐማርያም
16. አቶ አሰፋ ሀሐወልድ
17. አቶ ብሩክ ከበደ
18. አቶ ታምራት ታረቀኝ
19. አቶ አንዱአለም አራጌ
20. ወሐሮ ንግስት ገሐሕይወት
21. አቶ ደበበ እሸቱ
22. አቶ የኔነህ ሙላቱ
23. አቶ ማሙሸት አማረ
24. መሐቃ አለማየሁ የኔነህ -በአብላጫ ድምፅ የሚከላከል?
25. አቶ በድሩ አደም
26. አቶ አንተነህ ሙሉጌታ
27. አቶ መላኩ ፋንታዬ
28. መሐቃ ግርማ አማረ
29. አቶ ዳንኤል በቀለ -በአብላጫ ድምፅ የሚከላከል?
30. አቶ ነፃነት ደምሴ -በአብላጫ ድምፅ የሚከላከል?
31. አቶ መስፍን ዴቤሳ
32. አቶ ብርሀኑ አለማየሁ
33. አቶ ውድነህ ጀዲ
34. አቶ መላኩ ኡንቻ
35. አቶ አብዮት ዋቅጅራ
36. አቶ መብራቱ ከበደ
37. አቶ ዳንኤል በሪሁን
38. ወት ቅድስት በቀለ

39. አቶ ተስፋዬ ታሪኩ

40. አቶ ዋልታ ንጉስ አስናቀ

41. አቶ ሙሉ ጋሹ

ከነዚህ ተከሳሾች በተጨማሪ በ1ኛው ክስ የቀረበባቸውን ክስ ይከላከሉ የተባሉ ነገር ግን በሌሉበት ጉዳያቸው እየታየ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በህጉ መሰረት ጥፋተኛ ያለቸው

1. አቶ መስፍን አማን
2. አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ
3. አቶ ኤልያስ ክፍሌ ናቸው።

በ1ኛው ክስ ቀርቦባቸው ፍርድ ቤቱ ሊያስጠይቃቸው የሚችለው በተከሰሱበት አንቀፅ 238 ሳይሆን በአንቀፅ 257 ሆኖ ስላገኘውና ይህም እስከ አስር አመት የሚያስቀጣ በመሆኑ በህጉ መሰረት ቤሉበት ጉዳያቸው ሊታይ ስለማይችል አሁን የቀረበባቸው ክስ እንዲቋረጥ ትእዛዝ ሰጥቷል። እነዚህም

1. ዶር ነገደ ጎበዜ
2. አቶ ያሬድ ጥበቡ
3. አቶ ዳዊት ከበደ
4. አቶ አረጋዊ በርሄ
5. ዶር ታዬ ወሐሰማያት ናቸው።

ፍርድ ቤቱ በሌሎቹ ክሶች ወደፊት የሚሰጠው ብይን እንደተጠበቀ ሆኖ በ1ኛው ክስ የቀረበባቸውን ወንጀል መከላከል አያስፈልጋቸውም ያላቸው

1. አቶ ስለሺ አንዳርጌ
2. አቶ ሀብታሙ ገሐሕይወት
3. አቶ አስራት ጣሴ
4. ኮል ታምሩ ጉልላት
5. አቶ በቀለ ግርማ
6. አቶ ታዴዎስ በየነ
7. አቶ አለማየሁ መሰለ
8. ወት ሰብለወርቅ ታደሰ

9. አቶ እስክንድር ነጋ
10. አቶ ሰሎሞን በቀለ
11. አቶ ክፍሉ ታደሰ
12. አቶ ብርሃነ መዋ
13. ዶር ማሞ ሙጬ
14. አቶ አብርሃ በላይ
15. ፐር ጌታቸው ኃይሌ
16. አቶ ምርጫው ስንሻው
17. አቶ ታማኝ በየነ
18. አቶ ሊሻን ግዛው
19. ዶር ሞገስ ገሐማሪያም
20. አቶ ፋሲካ በለጠ
21. አቶ ሰለሞን ተካልኝ
22. አቶ ከፈለኝ ማሞ
23. ዶር አሰፋ ነጋሽ
24. አቶ ጌታቸው ጋረደው
25. አቶ ክፍሌ ሙላት
26. አቶ ታዬ ጌታቸው
27. አቶ እዮብ በቀለ
28. አቶ መሀመድ ሰማን
29. አቶ ካሳ ታደሰ
30. አቶ ፍቃዱ አሰፋ
31. ወጣት ምናለ ገብሬ
32. አቶ ገዛኸኝ ተስፋዬ
33. አቶ ተስፋዬ ጋንታ
34. አቶ አንተነህ ጌትነት
35. አቶ ውድነህ ተመስገን
36. አቶ ወንድሜነህ ደሳለኝ ናቸው።

በተመሳሳይ አቶ ካሳሁን ከበደ ከ1ኛ ክስ መከላከል አያስፈልገውም የተባለ በመሆኑና ሌላ የቀረበት ክስ ባለመኖሩ በነፃ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ተሰጥቷል።